# ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org

የሐዘን መግለጫ

ከትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ
ጁላይ 26፣ 2018
ዋሽንግተን ዲሲ

ለሀገራዊ አንድነታችን፣ ክብራችን እና ተስፋችን አመልካች ከሆኑ አንጡራ ተቋማት አንዱ የሆነውን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የፕሮጄክት ዋና ስራ አስኪያጅ እና የውድ ሀገራዊ ጀግናችን የኢንጂነር ስመኘው በቀለ ህልፈተ ህይወት ሰምተን ከባድ ሐዘን ላይ እንገኛለን። ሀገራችን ብርቅዬ ልጇን አጥታለች። የማሕበራችን ኣባላት ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል። የማሕበራችን አባላት የግድቡ ግንባታ እንዲፋጠን ከቦንድ ግዢ ባለፈ፤ እቦታው ደረስ በመገኘት ከኢንጂነር ስመኘው ስለ ግድቡ ጥቅም እና ታሪካዊ ፋይዳ ትምህርት ቀስመዋል። በዚህም የተነሳ እንጂነር ስመኘው በቀለ ለማሕበራችን እና አባላቱ እጅግ ቅርብ እና ውድ ነበሩ። በኢንጂነር ስመኘው በቀለ ሕልፈት ኢትዮጵያ ውድ የልማት እና የይቻላል ባይነት መንፈስ ምልክቷን አጥታለች። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በተባባረ የህዝቦች ክንድ ለፍጻሜ መድረሱ አይቀሬ ነው። የኢንጂነር ስመኘው ስራ በትውልዶች ማህደር ሁሌ ህያው ሆኖ ይኖራል። ማሕበራችን ለኢንጂነር ስመኘው በቀለ ቤተሰብ፣ ለወዳጅ ዘመድ፣ እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትን ይመኛል።

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ
ዋሽንግተን ዲሲ